# ምዕራፍ 11

## ጊዜ

## 11.1 በቀን ውስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያት

### የቡድን ሥራ ❶

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

1. የመኝታ ጊዜአችሁን ግለፁ፡፡
2. ወደ ትምህርት ቤት የምትመጡበትን ጊዜ ግለፁ፡፡
3. ፀሐይ የምትወጣው ጧት ነው ወይስ ማታ? የምትጠልቀውስ?
4. ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ያለው ጊዜ ቀን ወይስ ማታ ይባላል? ፀሐይ ወጥታ እያለችስ ያለው ጊዜ ምን ይባላል?

አንድን ቀን በብዙ ቦታ ከፋፍለን መግለጽ እንችላለን፡፡ ከነዚህም ጠዋት፣ እኩለ ቀን፣ ማታ ወይም ሌሊትና እኩለ ሌሊት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ፀሐይ አንዴ ወጥታ፣ ጠልቃ፣ ተመልሳ እስክትወጣ ያለው ጊዜ አንድ ቀን ተብሎ ይታወቃል፡፡ እያንዳንዱ ቀን 24 ሰዓቶች አሉት፡፡ የተለያዩ ዓይነት የሰዓት መቁጠሪያዎች አሉ፡፡ ቀጥለው የሚታዩት የሰዓት መቁጠሪያ ምሥሎች ናቸው፡፡






# 11.2 የሳምንቱ ቀኖች

ከላይ አንድ ቀን በ24 ሰዓቶች እንደሚከፋፈል አይተናል፡፡ ይኸም ማለት 24 ሰዓቶች አንድ ቀን እንደሚሆኑ ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ 7 ቀኖች አንድ ሳምንት ይሆናሉ፡፡ የሳምንቱም ቀኖች የየራሳቸው ስም አላቸው፡፡

## የቡድን ሥራ ❸

**የሚከተሉትን የሳምንቱን ቀኖች በቅደም ተከተል ስማቸውን አጥኑ፡፡**

| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሑድ |
|---|---|---|---|---|---|---|

### መዝሙር

*የሚከተለውን በቡድን በመሆን በመዝሙር መልክ ዘምሩ፡፡*




**መዝሙር**

ሰኞ ማክሰኞ

ሳልማር ቀርቼ እኔ አልሆንም ሞኞ፡፡

ረቡዕ፣ ሐሙስና አርብ፣

ትምህርት የአእምሮ ቀለብ፡፡

ቅዳሜና እሁድ፣

አስቀድሜ የተማርኩትን አጠናለሁ በዕቅድ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be reprinted

# የማጠቃለያ መልመጃ

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ሁለት ቀኖች ስንት ሰዓቶች ይሆናሉ?
2. ሁለት ሳምንቶች ስንት ቀኖች ይሆናሉ?
3. ትምህርት ቤት የምትሄዱት መቼ መቼ ነው? በየትኞቹ ቀኖች?
4. ትምህርት ቤት የማትመጡባቸው ቀኖች የትኞቹ ናቸው?
5. 3 ቀናት + 2 ቀናት = ______ ቀናት
6. 1 ሳምንት + 1 ሳምንት = ________ሳምንቶች
7. ሶስት ሳምንቶች ስንት ቀናት አሏቸው?
8. ሶስት ቀናት ስንት ሰዓት ይሆናል?
9. ፀሐይ በጠለቀች ጊዜ ብርሃን የምናገኘው ከምንድን ነው?
10. በአንድ ሳምንት ውስጥ ስንት እኩለ ቀናት አሉ?

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished